ወንጀልም ሆነ ዝምድና መቁረጥ የሌለበትን ዱዓ የሚያደርግ አንድም ሙስሊም የለም በዛች ዱዓው ምክንያት አላህ ከሶስት ነገሮች አንዱን የሚሰጠው ቢሆን እንጂ: ወይ የለመነው በፍጥነት ይሰጠዋል ፤ ወይ ልመናው ለመጪው ዓለም መልካም ምንዳ ማደለቢያ ይሆንለታል፤ ወይም የለመነውን ጉዳይ የሚያክል መጥፎ ነገር ከሱ ዞር ያስደርግለታል። " ሶሀቦችም " ስለዚህ (ዱዓእ) እናብዛ?" አሉ። እሳቸውም "(ዱዓእ ካበዛችሁ) የአላህ ስጦታም እጅግ ይበዛል።" አሏቸው።

ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ
ይስፈን) እንዲህ ብለዋል፦ «ወንጀልም ሆነ ዝምድና መቁረጥ የሌለበትን ዱዓ የሚያደርግ አንድም ሙስሊም የለም በዛች ዱዓው ምክንያት አላህ ከሶስት ነገሮች አንዱን የሚሰጠው ቢሆን እንጂ: ወይ የለመነው በፍጥነት ይሰጠዋል ፤ ወይ ልመናው ለመጪው ዓለም መልካም ምንዳ ማደለቢያ ይሆንለታል፤ ወይም የለመነውን ጉዳይ የሚያክል መጥፎ ነገር ከሱ ዞር ያስደርግለታል። " ሶሀቦችም " ስለዚህ (ዱዓእ)
እናብዛ?" አሉ። እሳቸውም "(ዱዓእ ካበዛችሁ) የአላህ ስጦታም እጅግ ይበዛል።" አሏቸው።» [ሶሒሕ ነው።] [አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) አንድ ሙስሊም ወንጀልና በደል ለመፈፀም እንዲገራለት መለመንን የመሰለ ወንጀል ባልሆነ፤ በቅርብ ዘመዱና በልጆቹ ላይ እርግማን መለመንን የመሰለ ዝምድና መቁረጥ ባልሆነ ዱዓእ አላህን የለመነና የጠየቀ ጊዜ አላህ በዱዓው አማካይነት ከሶስት ነገሮች አንዱን ይሰጠዋል ብለው ተናገሩ፡ ወይ የለመነውን በፍጥነት ይሰጠዋል፤ ወይም የትንሳኤ ቀን ደረጃውን ከፍ እንዲያደርግለት ወይም እንዲታዘንለትና ወንጀሉን መማሪያ እንዲሆንለት አላህ ምንዳውን ያደልብለታል፤ ወይም የለመነውን የሚያክል የሆነ መጥፎን ነገር በዱንያው ውስጥ ይከላከልለታል። ሶሐቦችም ለነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) "ስለዚህ ከነዚህ ደረጃዎች አንዱን እንድናገኝ ዱዓን እናብዛ እንዴ?" አሉ። ነቢዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) "አላህ ዘንድ ያለው እናንተ ከምትጠይቁትም በላይ ትልቅና ብዙ ነው። የርሱ ስጦታ አያልቅምም አይቀንስምም።" አሏቸው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5100